# ★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞክራሲያ ልዩ ዕትም** **መጋቢት /ሚያዚያ 2005**


## *ቀን የሰጠው ቅል ድንጊያ ይሰብራል፤*

## *የወያኔ የክፍፍል ፖሊቲካና መዘዙ*

በቅርቡ ከቤኒሻንጉልና መተከል ክልል የአማራ ብሔር ተወላጆች በወያኔ ባለሥልጣናት በግፍ መባረራቸውን ተከትሎ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፤ የውጭ መንግሥታትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከፍተኛ ተቃውሞና ወገዛ ሲያደረጉ መቆየታቸው ይታወቃል። ይህ በአማራ ዜጎቻችን ላይ የደረሰው ግፍና በደል ብዙ ቁጣና ቁጭት የቀሰቀሰ ከመሆኑ ባሻገር ወያኔ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ እየተከተለ ያለው የክፍፍልና ሀገር የማጥፋት ፖሊሲ በኢትዮጵያዊነት ላይም ሆነ በአገር ሉዓላዊነትና በሕዝብ አንድነት ላይ እየፈጠረ ያለው ጠንቅና መዘዝ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያመላክት ሆኗል። ባለፉት 20 ዓመታት ወያኔ በፈጠረው የጎሳ ፖለቲካ እንዲሁም ቋንቋንና ብሔረሰብን መሠረት አድርጎ በተዋቀረ ክልል ምክንያት በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ህይወታቸውን ማጣታቸው፤ ከቤት ንብረታቸውና ከቀያቸው መፈናቀላቸውና መሰደዳቸው ታሪክ የመዘገበው ነው። ሁሉንም መዘርዘር ባይቻልም የተወሰኑትን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። በአርባጉጉ ፤ በበደኖ፤ በአሰቦት፤ በአሰሳ አማሮች ተጨፍጭፈዋል፤ ከቤት ንብረታቸው ተባረዋል። ከባሌ ከአርሲና ከሐረር የአማራውም ሆነ የሌሎች ብሔረሰብ አባላት ከቀያቸው ተፈናቅለዋል። ከጋምቤላ አማሮችን ለማስወጣት ሙከራ ተደርጓል። ደቡብ ውስጥ በጉጂና በጌዲዮ፣ በጉጂና በቦረና ፣ በቦረናና በገሪ መካከል ግጭቶች ተፈጥረዋል፤ የሲዳማ ብሔረሰብ በደቡብ ክልል ውስጥ መጠቃለሉን ተቃውሟል፤ የስልጢ ብሔረሰብም ጉራጌ አይደለንም በማለት የመገንጠል እንቅስቃሴ አድርጎ ተግባራዊ ሆኗል፤ ከደቡብ ክልል ቢንች ማጂ ዞን ከጉራፈርዳ ወረዳ አማሮች ተባረዋል፤ ሐረር ውስጥ በሐረሪና በኦሮሞ መካከል ግጭት ተፈጥሯል ፤ በአሰሳ በበርታ፣ በኦሮሞና በአማራ ብሔረሰቦች መካከል በተለያየ ጊዜ ግጭት ተቀስቅሶ በርካታ ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል ወዘተ... ወዘተ....። ለዚህ ሁሉ ምስቅልቅል ሁኔታ ምክንያትና ምንጩ የወያኔ የክፍፍል ፖለቲካና አለተቀናቃኝ በሥልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ ለመቆየት የቀየሰው ቋንቋንና ብሔረሰብን መሠረት ያደረገው የክልል ፌዴሬሽን ነው። ይህ የክፍፍል ፖሊሲ የኢትዮጵያን የረጅም ጊዜ ታሪክ የሚክድ ሲሆን አገሪቷ በ1982 ዓ.ም. የተለያዩ ብሔረሰቦች አድቦልቡለው የሠሯት ግን በማናቸውም

ጊዜ ሊያፈርሷት የሚችሉ አዲስ አገር ነች በሚለው ፍልስፍና ተመስርቶ  የተቀረጸ ነው። ይህ የከፍፍል ፖሊሲ ለአገርና ለሕዝብ አንድነት እንዲሁም ለኢትዮጵያዊነት ስሜት ቋሚ ጠንቅ  ከመሆኑ ባሻገር የወያኔን ጸረ ኢትዮጵያዊነት በማያወላውል መንገድ ያረጋግጣል። ትግራይን ለማስገንጠል የተመሠረተውና ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም ብሎ  አቋም ይዞ፤ ቀስቅሶና ታግሎ በተግባር እንድትገነጠል ያደረገው ወያኔ በሚኒልክ ወረራ የተፈጠረችው ኢትዮጵያ የመቶ ዓመት ታሪክ ብቻ ነው ያላት  በሚል ማጠያቂያ የጠነሰሰውን የከፍፍል ፖሊሲ መሠረት ቢስነት ለማስረዳት ስለ አገር ምንነትና ምስረታ ጥቂት ግንዛቤ መስጠት አስፈላጊ ይሆናል።

አገር በአንድ አካባቢ የተለያዩ ስዎች በአንድነት በመኖር የሚፈጥሩት የእርስ በርስ ትሥሥርና አደረጃጀት ሲሆን በአሁኑ ወቅት በአለም ላይ ነጻ ከሚባሉት ወደ 200 ከሚደርሱ ሀገራት ውስጥ አብዛኞቹ አሁን ያላቸውን ዘመናዊ የመልክአምድር ቅርጽ ሊይዙ የቻሉት በመቶና በሺ ዘመናት በሚቆጠሩ  የታሪክ ክስተቶች ውስጥ በማለፍ ነው። የእያንዳንዱን አገር ታሪክ ብንመረመር በዜጎች መካከል ትስስር የፈጠሩ የተለያዩ ምክንያቶች  እንደነበሩም እንረዳለን። ጦርነቶች፤ የንግድ ልውውጦች ፤ የሃይማኖት መስፋፋት፤ በንጉስ ወይም በመሪ መወረርና መተዳደር፤ የጋብቻና የባህል ትስስር ወዘተ... ከብዙዎቹ ውስጥ ጥቂቶቹ ሲሆኑ ዜጎች ለረጅም ዘመናት አብረው በመኖራቸውና በተለያዩ ምክንያቶች በመያያዛቸው  አንድ አገር አንድ ሕዝብ የሚለውን ስሜት በስነ ልቦናቸው ፈጥረው  አብረው መኖር ችለዋል። አንድ አይነት ቋንቋ መናገር ለሀገር መመሥረት ብቸኛ ምክንያት አይደለም። በአንዳንድ ቦታዎች አገር አንድ ቋንቋ በሚናገሩ ዜጎች ብቻ  ሲገነባ በሌሎች ቦታዎች ለምሳሌ እንደ ህንድ አይነት በመንግሥት ደረጃ የሚታወቁ ከአራት መቶ ቋንቋዎች በላይ እንዳሉ መረዳት ይቻላል። እንግሊዝ አሜሪካ ካናዳ አውስትራሊያና ኒው ዚላንድ ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ቢሆንም የተለያዩ አገሮች ናቸው፤ አንድ አይነት ቋንቋ የሚናገሩ  አብዛኞቹ የደቡብ አሜሪካ አገሮች ወሰንተኛ ቢሆኑም በተለያዩ አገሮች ተከፋፍለዋል፤ እዚሁ አጠገባችን ያለችው ሶማሊያም በቋንቋም ሆነ በዘርና በሃይማኖት አንድ ሆነው መከፋፈላቸው የማይካድ እውነታ ነው። ባህል፤ ሃይማኖት ወዘተ... ለአገሮች መመሥረቻ ብቸኛ ምክንያቶች አይደሉም። በተለያዩ አገሮች የተለያዩ ሃይማኖትን የሚከተሉም ሆነ የተለያዩ ባህሎች ያሏቸው ዜጎች አብረው ሲኖሩ እናያለንና ። ለሀገሮች  መመሥረት ዋናውና መሠረቱ አንድ ነን የጋራ ታሪክ አለን በሺ ክሮች ተሳስረናል ወዘተ... የሚለው  አብሮ የመኖር ሥነ ልቦናዊ ስሜት ነው። ይህ ስሜት ሊቀረጽ የሚችለው ደግሞ ለረዥም ጊዜ አብሮ በመኖር፤ ባህልን ቋንቋን ልማድን ወዘተ... በመወራረስ ነው። በጀርመን ሆነ በስዊስ በህንድ ሆነ በቻይና የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ የተለያዩ ሃይማኖትን የሚከተሉ ዜጎች አገሬ ብለው በአንድ ላይ የሚኖሩበትና በአገራቸው የሚኮሩበት ምክንያት የሚያስተሳስራቸው ብሔራዊ የአገር ስሜት በመኖሩ ምክንያት ነው።

ሀገራችንም ዘመናዊውን መልክ የያዘችው ከሌሎች በተለየ ሁኔታ አለመሆኑን እንገነዘባለን። ዘመናዊ ብሔራዊ መንግሥትና አስተዳደር የተቋቋመው ከሚኒሊክ ዘመን ጀምሮ መሆኑ የሚያከራክር ባይሆንም አገራችን አሁን ያላትን ቅርጽ ለመያዝ የበቃችው ከብዙ ሺ ዘመን በላይ ብዙ መልኮችና ቅርጾችን ያካታተውን የታሪክ ዘመን አሳልፋ ነው። እንደሌላው የዓለም ክፍል ሁሉ በአንድ ወቅት ወይም በሌላ አንድ ንጉስ ወይም የአገር መሪ የተወሰነውን ክፍል የማስተዳደር፤ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎችን ወርሮ የማስገበር ሂደቶች ተፈጽመዋል። በአንድ አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ በአንድ ወቅት አስገባሪ በሌላ ወቅት ገባሪ ሆኖ ኖሯል። ክልሎች ከጊዜ ወደጊዜ ሲሰፉና ሲጠቡ ቆይተዋል። ከሰሜን ነገሥታት ወደ ደቡብ በመዝመት ዜጎችን ወርረው በማስገበር በስራቸው እንዳደረጓቸው ሁሉ ከደቡብም እንደኦሮሞው እንቅስቃሴና ወይም እንደ ግራኝ መሀመድ ዓይነቶቹ ወደ ሰሜን በመዝመት ግዛቶችን በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ ሞክረዋል። አማራው አጼ ቴዎድሮስ የዘመቱት በትግሪኛ ወይም በኦሮምኛ ተናጋሪው ላይ ብቻ ሳይሆን በጎንደሩ፤ በጎጃሙ፤ በወሎውና በሸዋው አማራ ላይ ነው፤ የትግራዩም አጼ ዮሐንስ ያስገበሩት አማራውን ወይም አፋሩን ብቻ ሳይሆን ትግሪኛ ተናጋሪውንም ጭምር ነው። በዚህ የረጅም ዘመን የታሪክ ሂደት ብዙ ጦርነቶች ተካሄደዋል፤ ብዙ እልቂቶችም ደርሰዋል። ይሁን እንጅ ይህ የረጅም ዘመን የጦርነት ታሪክ የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርስ አጋምዶታል። በንግድ ግንኙነት፤ በሃይማኖት ማስፋፋት፤ በሕዝብ ዝውውር፤ በስደት፤ በጋብቻ ወዘተ… በሕዝብ መካከል የተደረጉት እንቅስቃሴዎች ቋንቋ ባህልና ልማዱ እንዲወራረስ አድርጓል። ይህም በሕዝቦች መካከል የነበረው የረዥም ጊዜ መስተጋብር ለዛሬዋም ኢትዮጵያ መሠረት ሆኗል። ይህ የጋራ ታሪክና የእርስ በርስ ግንኙነትና ትሥሥር በአንደነት በአገር አብሮ በመኖር ከሚገኘው መሠረታዊ ጥቅም ጋር ተዳምሮ ነው ኢትዮጵያዊ ነን የሚለውን አገራዊ ስሜት በእያንዳንዱ ዜጋ ሥነ ልቡና ውስጥ ሊፈጥር የቻለው። አገራችን ኢትዮጵያ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን የስብዕናችን፤ የክብራችን ፤ የወጋችን የባህላችን የማንነታችን መግለጫ ነች።

ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር እውን ከሆነባት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያውያን በሰላምና በአንድነት ኑረዋል። በአድዋ የውጭ ወራሪዎችን መክተው የአገራቸውን ነጻነት አስጠብቀዋል። በ1928 ጣሊያን በወረረበት ጊዜም ኢትዮጵያውያን በቋንቋ፤ በዘር በሃይማኖት የተከፋፈሉበት ሁኔታ ሳይሆን አምስት ዓመት ሙሉ በጀግንነት፤ በዋና መልኩ አንድ ላይ በመቆም ወራሪውን ጠላት አስወግደዋል። የትግራይ ሆነ የአማራ፤ የኦሮሞ ሆነ የወላይታ፤ የአፋር ሆነ የጉምዝ፤ የሃድያ ሆነ የሶማሌ ዜጎች በአንድነት የውጭ ጠላትን በመመከት አገረቷን እንደ አገር አቆይተዋል። ለዚህም ታሪክን መጥቀስና የአርበኞችን ስም መዘከር ይቻላል።

ይህ በረጅም ጊዜ የተገነባው አገራዊ ስሜት በማናቸውም ጊዜ እንከንና እንቅፋት አልነበረውም ማለት አይቻልም። አንድነትን የሚያጎለብቱና የሚያጠናክሩ፤ የሚያጋምዱና የሚያስተሳስሩ በርካታ ሁኔታዎች እንደመኖራቸው ሁሉ አንድነትን የሚያላሉ፤ የአገሪቷን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ሁኔታዎችም እንደነበሩ ታሪካችን የሚመሰክረው ነው። ሁሉም ብሔርና ብሔረሰብ በእኩል ደረጃ መብቱ ተጠብቆለት ኑሯል ማለት አይቻልም። ጭቆናውን ያካሄዱት በሥልጣን ላይ የነበሩት ጥቂት ግለሰቦች ቢሆኑም በርከት ያሉት ብሔርና ብሔረሰቦች ተጨቁነው መቆየታቸውና ከዚህ ጭቆናም ለመላቀቅ ትግሎች ማካሄዳቸው የማንክደው የታሪካችን ገጽታ ነው። አሮሞውና በደቡብ ያሉ ብሔረሰቦች መሬታቸውን ተነጥቀው በፊውዳሎቹ በመብዝበዛቸው ምክንያት የመሬት ላራሹ ጥያቄ በወቅቱ በነበረው ተማሪዎችና ተራማጅ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎችም ተነስቶ ትግል ተካሄዶበታል። አሮሞው፤ በደቡብ ያሉ የተለያዩ ብሔረሰቦች፤ አፋሩ፤ ሶማሌው ትግሬው ወዘተ.... ኤርትራን ጨምሮ ባህላችንና ቋንቋችን ይከበር፤ የራስን እደል በራስ የመወሰን መብታችን ይከበር በሚል ጥያቄ አቅርበዋል፤ ትግል አካሂደዋል። በአጼውም ዘመን ሆነ በደርግ እንዲሁም በወያኔ በርካታ የብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች ተካሂደዋል፤ እየተካሄዱም ናቸው። የምዕራብ ሶማሌ ነጻ አውጭ ድርጅት፤ የእነዋቆ ጎቱ እንቅስቃሴ፤ የእነታደሰ ብሩ፤ የኦነግ፤ የኤርትራው፤ የወያኔ ወዘተ.... ሁሉ በብሔርና ብሔረሰብና በአጠቃላይ ጭቆና ላይ ተመሥርተው የተካሄዱ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ህይወት ዋጋ ያስከፈሉ እንቅስቃሴዎች ነበሩ። እነዚህም ተቃውሞዎች በየጊዜው የነበሩ አገዛዞች ተገቢ መፍትሔ ሊሰጧቸው ባለመቻሉ ችግሩ ከመባባሱም ሌላ በአገሪቷ ህልውና ላይ ከፍተኛ አደጋ እንዲንዣበብ አድርጓል።

በስድሳዎቹና በሰባዎቹ ዓመታት ወጣት ተማሪዎች እንዲሁም በኋላም በኢሕአፓና በሌሎች ተራማጅ ድርጅቶች ውስጥ ተካትተው ለሥርዓት ለውጥ የታገሉት ወጣቶች የብሔር ጥያቄን አንስተው የብሔር ጭቆና ይወገድ፤ ለብሔርና ብሔረሰብ ጥያቄ ተገቢው ዴሞክራሲያዊ መልስ ይሰጠው የሚለውን አቋም የገፉት ጥያቄው ተገቢ መልስ ካላገኘ በኢትዮጵያዊነት ስሜት ላይና በአገሪቱ ህልውና ላይ አደጋ ያመጣል ከሚል ስጋትን ካዘለ እምነት ነበር ። የተራማጁ ክፍል ጥያቄ በዘመኑ በግራው ርእዮተ ዓለም ንድፈ ሀሳብ ተሸፍኖ የነበረውን የጠባብ ብሔረተኛ አደጋን በቂ ትኩረት አለመስጠቱ ድክመት ቢሆንም በወቅቱ የችግሩን መኖር ማመልከቱና ተገቢ መፍትሔ እንዲሰጠው መታገሉ የሰጎን ፖለቲካ ለማይፈልጉ ሁሉ ትክክል ነበር ። በተከታታይ የነበሩት አገዛዞች ጭቆናው ይወገድ እኩልነት ይኑር ለሚለው የፍትህ ጥያቄ ተገቢ መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ ተቃውሞውን ለማፈን የወሰዱት የኃይል እርምጃ ችግሩን አባባሰው እንጅ አልፈታውም። ከብዙ ዓመታት ጦርነቶች፤ ከበርካታ ወገኖቻችን ህይወት መጥፋት ከብዙ ንብረትና ሀብት መውደም በኋላ የኤርትራ መገንጠል እውን የሆነውና የአገራችን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ የወደቀው በአንድ በኩል በአገዛዞቹ ተፈጥሮ ባህርይና ጠባይ ሲሆን በሌላ በኩል እንቅስቃሴውን እንመራለን በሚሉት

ብሔረተኛ ድርጅቶች ከነበረው ጠባብ አመለካከት የመነጨ ነው። ጭቆናው ተወግዶ፤ እኩልነት ሰፍኖ የሕዝብና የአገር አንድነት ሊጠበቅ ይችል የነበረው በዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ብቻ ነበር። የነበሩት አገዛዞች ደግሞ ከዴሞክራሲ ጋር የማይተዋወቁ አምባገነን አገዛዞች ስለነበሩ በየብሔርና ብሔረሰቦቹ የተነሳው የፍትህና የእኩልነት ጥያቄ መልስ ሊያገኝ አልቻለም። ችግሩን ለመፍታት በሚል በአምባገነን አገዛዞች የተወሰዱት የጦርነት መፍትሔዎች ችግሩን የበለጠ አባባሱት እንጂ ሊፈቱት አልቻሉም። ጦርነቶቹን በግምባር ቀደምትነት እንመራለን የሚሉትን ጠባብ ብሔረተኛ ድርጅቶችን ክንድ አፈረጠሙ እንጅ ተቃውሞው እንዲዳከም አላደረጉም።

ከላይ እንደተጠቀሰው በተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል ለዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የቋንቋ፤ የባህል፤ የሃይማኖት፤ የልምድ የጋብቻ ወዘተ... መተሳሰርና መጋመድ ለዘመናት የሰረጸ ስለሆነ በየጊዜው በደልና ብሶት ቢኖርም በሕዝባችን መካከል ወደመለያየት የሚያደርስ መሠረታዊ ምክንያት አልነበረም። በአገዛዞች የተፈጠረው በደልና ጭቆና በወቅቱ መልስ ሳያገኝ ቀርቶ ከጊዜ ወደጊዜ ከተከመረ በገዥዎች ከተራገበና ከተባባሰ የብሔርተኞች ፍላጎት ማሚያ ሆኖ ወደ መለያየት ሊያደርስ ይችላል። የእኩልነቱም ሆነ የፍትሕ ጥያቄ የሚነሳውና የሚመለከተው ብዙኃኑን ዜጋ ቢሆንም ተቃውሞው መልክ ይዞ በተደራጀ መልክ የሚካሄደው በተወሰኑ ብሔረተኛነት ባጠቃቸው ቡድኖች ነው። አብዛኛውን ጊዜ ተቃውሞውን በግምባር ቀደምትነት የሚመሩት የተደራጁ ቡድኖች ደግሞ ከሕዝቡ ጥያቄ ይልቅ የሚታያቸው ሥልጣን ይዞ የግል ጥቅምን መግፋት ስለሆነ በሚገነጠለው አካባቢ ራሳቸውን ሥልጣን ላይ ለማቆየት ዋስትና እስካገኙ ድረስ መገንጠልን ይገፋሉ። ይህ በሌሎች አገሮች የደረሰ ነው፤ በእኛም አገር የኤርትራ መገንጠል በተግባር የዋለው በዚህ ምክንያት ነው። ኣንዳንዶችም እንገንጠል ሲሉ የሚመኙት ይህንን ነው።

አረመኔው ደርግ ከሕዝብ ተነጥሎ ጉልበቱ በዛለበት ወቅት በለስ የቀናው ወያኔ በወታደራዊ ኃይልና በባዕዳን ትብብር ሥልጣን ሲይዝ በአገሪቷ ውስጥ መፍትሔ ይሹ ከነበሩት በርካታና ውስብስብ ችግሮች መካከል አንዱ የብሔርና ብሔረሰብ ጥያቄ እንደነበር ግልጽ ነው። ወያኔ ለጥያቄው መፍትሔ ይሆናል ብሎ ያቀረበው የቋንቋ ክልሎችን መሠረት ያደረገው ፌዴራል ሥርዓትና በሕገ መንግሥት ተብየው ውስጥ የተካተተው የመገንጠል መብት ችግሩን ከማባባስ አልፎ የሀገሪቷን ህልውናና የሕዝቧን አንድነት ከምንጊዜውም በላይ አደጋ ውስጥ እንዲገባ ያደረገ ነው። ትግራይን ለመገንጠል ተመሥርቶና ተንቀሳቅሶ የነበረው ወያኔ በወታደራዊ ኃይልና በባዕዳን ድጋፍ አገሪቷን በተቆጣጠረበት ወቅት ኢትዮጵያን ከፋፍሎና አዳክሞ በሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችለው ሁኔታ መኖሩን ሲገነዘብ የመገንጠል አቋሙን አሸጋሸገ። ጠባብ መሠረት ያለው ቡድን ፍላጎቱንና አገዛዙን በብዙኃኑ ላይ እየጫነ ለረጅም ጊዜ በሥልጣን ላይ ሊቆይ እንደማይችል ገና ከመጀመሪያው ግልጽ የሆነለት ወያኔ ሥልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ ለመቆየት

የሚያስችሉትን ስልቶች መቀየስ ነበረበት። በምዕራባውያን ምክርና ትብብር ተግባራዊ እንዲሆኑ የቀረቡት ኤርትራን ከማስገንጠል በተጨማሪ የመገንጠልን መብት በሕገ መንግሥት ተብየው ውስጥ ማካተትና አገሪቱን በቋንቋንና በብሔር ክልሎች በመከፋፈል በመሪ ድርጅት የሚዘወር ሥልጣን አልባ፤ መብት አልባ የሆነ የቋንቋ ፌዴሬሽን መመሥረት ነበር። የኤርትራ ጉዳይ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሕዝቡ ተወያይቶበትና ሀሳብ ሰጥቶበት ውሳኔም አሳልፎበት እንዲፈታ ከማድረግ ይልቅ ለመገንጠሉ ዋና ተከራካሪና ጠበቃ ሆኖ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ደብዳቤ በመጻፍ ሻዕቢያ ኤርትራን እንዲገነጥል ተባብሯል፤ ኢትዮጵያንም አንድ አካሏ እንዲቆረስ ከማድረግ ጋር አለወደብ አስቀርቷታል።

የመገንጠልን መብት የሚፈቅደውን አንቀጽ 39 ን ሕገ መንግስት ተብየው ውስጥ ወያኔ እንዲካተት ያደረገው ባንድ በኩል መገንጠልን የሚመኙ ብሔረተኛ ድርጅቶች ሁል ጊዜ በህልም እንጀራ እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱ ህልውናና የሕዝቦቿ አንድነት አደጋ ላይ መውደቁ የሚያስጨንቀው ወገን ወያኔ ከሌለ አገሪቱ ትበታተናለች የሚል ስጋት ውስጥ ገብቶ በአገዛዙ ላይ የሚያደርገውን ተቃውሞ እንዲያለዝብ የተደረገ ተንኮል ነው። አገሪቱን በቋንቋ ክልሎች በመከፋፈል እንዲሁም በብሔረሰቦች መካከል የጥላቻ መርዝ እንዲዘራ ያወጣውና በተግባር ያዋለው ፖሊሲ ደግሞ በተለያየ መንገድ ተሳስሮና ተጋምዶ የነበረው ሕዝብ አንድነቱ እንዲላላ፤ ተነጣጥሎ እንዲዳከም፤ ለአገሩም ሆነ ለመብቱ በአንድነት ቆሞ ጠንካራ ብትር በአገዛዙ ላይ እንዳያሳርፍ ለመከላከል የጠነሰሰ ስልት ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በየብሔረሰቡ ያሉት ብሔረተኛ ድርጅቶች ተጠናክረው የሥልጣን ተቀናቃኝ እንዳይሆኑ ወያኔ በአንድ በኩል የራሱን ወታደራዊና የጸጥታ መዋቅር በየክልሉ ከማጠናከሩ ጎን ለጎን በጥቅም በሹመት የተደለሉ የተለጣፊ ድርጅቶች አባላትን አሰባስቦና የራሱ አሽከር፤ሎሌና ተባባሪ በማድረግ ተገንጣይም ሆነ ተቃዋሚ የሆኑ ብሔረተኛ ድርጅቶችንም ከሕዝቡ ለመነጠልም ሆነ በይዞታ እንዲዳከሙ ለማድረግ ሞክሯል። ይህም የፓለቲካ መረጋጋትን ለማስገኘት አንድ የተጠናከረ ድርጅት ብቻ ያስፈልጋል ከሚለው በ1982 ዓ.ም ሲዘነዘር ከነበረው የምዕራባውያን ምክር ጋር አብሮ የሚሄድ ስልት ነበር።

በ1928 ጣሊያን ከነደፈው የክፍፍል መልክአ ምድር ተገልብጦና ተስተካክሎ በቋንቋና በብሔረሰብ ላይ ተመሥርቶ የተቀረጸው የብሔር/ብሔረሰብ ፌዴሬሽን ባንድ በኩል ለተባሉት ብሔርና ብሔረሰቦች የሰጣቸው ይህ ነው የሚባል መብትም ሆነ ሥልጣን የሌለ ሲሆን በሌላ በኩል ግን ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ተሳስሮ በነበረው በኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ላይና በአገሪቷም ህልውና ላይ ምን ጊዜም ሊፈነዳ የሚችል ፈንጂ ቀብሯል። ክልሎቹ የተከለሉት በጥናት ላይ በተመሰረተ እውነታ እንዲሁም በሕዝብ ፍላጎትና ይሁንታ ሳይሆን በአምባገነንነትና በማናለብኝነት ነው። ዘጠኝ ከሚባሉት ክልሎች መካከል አራቱ ማለትም የደቡብ፤ የጋምቤላ፤ የቤኒሻንጉል ጉምዝና የሐረሪ ክልሎች የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ብሔርና

ብሔረሰቦች የሚኖሩባቸው አካባቢዎች ናቸው። አራቱ ደግሞ የትግራዩ፤ የአማራው፤ የኦሮሞውና የሱማሌ ክልሎች አንዱ ቋንቋ ተናጋሪ በቁጥር ቢበዛም ውህዳን የሆኑ ግን ቁጥራቸው ቀላል ግምት የማይሰጠው የሌሎች ብሔረሰብ አባላት አብረው የሚኖሩበት መሆኑ ግልጽ ነው። የቋንቋው ፌዴሬሽን ለየክልሉ ብሔርና ብሔረሰቦች ያመጣው ነገር ቢኖር የክልል ባለሥልጣናት በአዲስ መልክ በየክልሉ ያሉ ውህዳን ብሔረሰቦች አባላትን መጨቆንና ማሰቃየት ብቻ ነው። ወያኔ በክልሎች ውስጥ አስተዳደሩን በተለጣፊዎቹ አለዚያም በቀጥታ በካድሬዎቹ አማካይነት የሚያካሂድ ሲሆን የክልሉንም ንብረት ሆነ ሀብት በቀጥታ የሚበዘብዝበትን መንገድ አመቻችቷል። ለምሳሌ መሬት በመንግሥት ቁጥጥር ስር እንዲውል በሕገ መንግሥት ተብየው ደንግጎ በፌዴራል መንግሥት ስም በየክልሉ ያለውን መሬት እንዳሻው እየቸበቸበ ከፍተኛ ሀብት በማካበት ላይ ይገኛል። ተለጣፊዎቹ ግምባር ቀደም ድርጅት ነኝ ከሚለው ከወያኔ ጋር በማበር የጥቅምና የሥልጣን ተጋሪ ሆኑ እንጅ የየትኛውም ብሔረሰብ አባል በወያኔና በተባባሪዎቹ ከመጨቆንና ከመበዝበዝ ያመለጠ የለም።

የክልል ፌዴሬሽን በሀገሪቱ ልዕልናና በሕዝቦቿ አንድነት ላይ ያመጣው ጠንቅ ግን ቀላል ግምት ሊሰጠው የሚችል አይደለም። ክልሎች ሲፈጠሩ እያንዳንዱ የክልል ባለሥልጣን በክልሉ ያሉ ውህዳን ብሔረሰብ አባላትን ጠርጎ የሚያስወጣ መብት ያለው ዓይነት ስሜት በመፍጠሩ በበደኖ፤ በአሰቦት፤ በአርባጉጉ፤ በአሶሳ፤ በኦጋዴን፤ በአዋሳ በጋምቤላና አሁን ደግሞ በጊሻንጉል ወዘተ... በአማራውና በሌሎች ብሔረሰቦች ላይ የደረሱ እልቂቶች ሊደርሱ ችለዋል። የእኩልነት ጥያቄ መመለሱ፤ በራስ ቋንቋ የመናገሩ፤ የራስን ባህል ልማድ ወዘተ... የማዳበሩ ክስተት የአንድነትንና የአብሮ መኖር ስሜትን ማጠናከር ሲገባው የጥላቻና የጎሳ ስሜትን እንዲፈጥር ከብሔርተኞች ግፊት እየተደረገ ነው። በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ወጣቶች ከሌላው የሕብረተሰብ ክፍል በተሻለ ሁኔታ እውቀት የገበዩ፤ የሀገርና የወገን ፍቅር ሊያንገበግባቸው የሚገባ፤ ለሕዝቦች አንድነትና እኩልነት ቅድሚያ ሰጥተው፤ ኃይላቸውን አስተባብረው በአምባገነኑ አገዛዝ ላይ ምት ማሳረፍ ሲገባቸው፤ በዘርና በቋንቋ ወገን ሲለያዩ በማይረባ ምክንያት በየጊዜው ሲጣሉ፤ ሲደባደቡ መታየታቸው የክፍፍሉ ጠንቅ ምን ያህል ስር እየሰደደ የመጣና አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያመለክት ነው። ባለፉት 20 ዓመታት ይህ አካባቢ ወይም ይህ ወሰን ለኔ ይገባኛል የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት በተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል የተካሄዱት ደም መፋሰስን ያስከተሉ ግጭቶች በቋንቋና በጎሳ ላይ የተመሰረተው ፌዴረሽን ያስከተለው ሌላው ጠንቅ ነው።

የሕዝብ መብት ተረጋግጦ የሕግ የበላይነት ዴሞክራሲና ነፃነት እውን እስካልሆኑ ድረስ አገራችን ውስጥ ያሉት ልዩ ልዩ ችግሮች እየተባባሱ መሄዳቸው ግልጽ ነው። የክፍፍል ፖሊሲን በመዘርጋት ወያኔ ለተወሰነ ጊዜ የሥልጣን ዕድሜ ቢያገኝም ሕዝብ ካመረረና ካመጸ ደግሞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊወገድ እንደሚችል

የአገራችንም ሆነ የሌሎች አገሮች ታሪኮች ያረጋግጡልናል። የከፍፍሉ ጠንቅ ወያኔ ሲወገድ ምን ዓይነት መልክ እንደሚያዝ መተንበይ ባይቻልም አደጋውን ግን ማቃለል አይቻልም።

ስለሆነም ምን መደረግ አለበት የሚለው ጥያቄ መልስ ፈላጊ ነው። ኢሕአፓ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ በዚህ በኩል አቋሙን የገለጸና የአብራራ ሲሆን የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት አሁንም በማያዳግም ሁኔታ ግልጽ ማድረግ ይሻል። መልሱም አመለካከትን ከማስተካከል ጀምሮ በተግባራዊ እንቅስቃሴዎች መፍትሔዎችን የመሻትና የረጅም ጊዜና የአጭር ጊዜ ተግባራትን ማከናወንን ያካትታል። በመጀመሪያ ደረጃ መታወቅ ያለበት ጥያቄ በሀገራችን ብሔርና ብሔረሰቦች የእኩልነት ጥያቄ ቢያነሱ፤ በራሳቸው ቋንቋ የመናገር፤ የራሳቸውን ባህል የማዳበር፤ በአካባቢያቸው ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ጥያቄም ማንሳታቸው ተገቢ ጥያቄ መሆኑና መልሱንም የይስሙላ ሳይሆን በተገቢው መንገድ ዴሞክራሲን መሠረት አድርጎ በሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። የእኩልነትና የፍትህ ጥያቄዎችን የሚያነሱ ብሔር/ብሔረሰቦች በጥላቻ የታጠሩ መገንጠልንም ሁሉም የሚሹ ናቸው ማለት አይደለም ። በአርባ ጉጉም ሆነ በበደኖ የደረሰውን እልቂት ያስቆሙ፤ ዜጎች ከተፈናቀሉበት ቀያቸው እንዲመለሱ ያደረጉ ለረጅም ጊዜ ከሌሎች ጋር አብረው የኖሩ የኦሮሞ አዛውንት አባቶች፤እናቶች መሆናቸውን ማስታወስ ያስፈልጋል። ስለሆነም የብሔርና/የብሔረ ሰብ ጥያቄዎች እንደሌሉ፤ በብሔርና/ብሔረሰቦች በኩል የእኩልነት ጥያቄ መነሳቱ ተገቢ እንዳልሆነ የሚመለከቱ ዜጎች አመለካከታቸውን ማስተካከል ያስፈልጋቸዋል። በአንጻሩም የብሔር/ብሔረሰቦችን የፍትሕና የእኩልነት ጥያቄ በመለጠጥ ከመገንጠል ጋር አያይዘው ጥያቄውን የራሳቸው ፍላጎትና አላማ ግብ መምቻ ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች የእኩልነት ጥያቄ ከተመለሰ በብሔርና ብሔረሰቦች መካከል ወደ ልዩነት የሚያመራ መሠረታዊ ቅራኔ አለመኖሩን መረዳት ይኖርባቸዋል።

እንደ ኢትዮጵያ የመሰሉ የብዙ ብሔርና ብሔረሰብ ያሉባት አገር ውስጥ የፌደራል ሥርዓት ጠቃሚነት ቀላል ግምት ሊሰጠው የሚችል አይደለም። ይሁን እንጂ የፌዴራል የአስተዳደር ክልሎች ሁሌም ቋንቋን ወይም ብሔርን መሠረት ባደረገ መካለል አይኖርባቸውም። በጥናት በውይይትና በመግባባት በመጨረሻም በሕዝብ ይሁንታ መደረግ ይኖርበታል። የየትኛውም ቋንቋ ተናጋሪ የየትኛው ብሔር/ብሔረሰብ አባል የሆኑ ኢትዮጵያውያን በየትኛውም የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የመኖር፤ ቤተ ስብ የመመስረት፤ የመሥራት ወዘተ... መብታቸው የተከበረና የማይገረሰስ ነው። ይህ በሁሉም ዜጎች ዘንድ ግንዛቤ ማግኘት ያለበት መሠረታዊ ጉዳይ ሲሆን በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ሕዝብን እወክላለሁ የሚል መንግሥት የሕዝብን መብት በማስከበር በኩል ካሉበት ኃላፊነቶች መካከል ዋነኛው ነው።

የብሔረሰቦች የእኩልነትና የፍትሕ ጥያቄ በትክክል ሊመለስ የሚችለውም ሆነ ማዕከላዊ የፌዴራል አስተዳደርና የአካባቢያዊ አስተዳደሮች ተግባራቸውና የሥልጣን ክፍፍላቸው ሚዛኑ ተጠብቆ፤ ሀገራችንም ህልውናዋና የግዛት አንደነቷ ተከብሮ ሁሉም ዜጋ በእኩልነት በሰላምና በብልጽግና ሊኖር የሚችለው መሠረታዊ የሆኑ የሕዝብ መብቶች የተከበሩበትና የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ብቻ ነው። ይህንኑ በውል በመረዳት ባጠቃላይ ሁላችን በሀገራችን ላይ የተጫነውን የወያኔ አምባገነን አገዛዝ በተባበረ ክንድ ለማስወገድ የረቀቀ ስልት መቀየስና ተጨባጭ ትግሎችን ማድረግ ይጠበቅብናል። ወያኔ የዘረጋብንን የክፍፍል መረብ ልንበጣጥስም ሆነ ያጠመደብንንም የመበተን ፈንጅ ልናመክን የምንችለው የአንዳችን ቁስል ለሁላችንም ሲሰማን፤ የአንዱ በደልና ብሶት የሁላችንም አደርገን ስንወስድ ነው። በዚህ በኩል በቅርቡ በሙስሊም ወንድሞቻችን እና በክርስቲያኑ መከካል እየተደረገ ያለው የትግል አጋርነት፤ በቤኒሻንጉልም ሆነ በጋምቤላ በአማራው ላይ የተወሰደውን የዘር ጠረጋን አስመልክቶ በሁሉም ወገኖች እየተሰማ ያለው የጋራ ተቃውሞ ፤ እንዲሁም በልዩ ልዩ ጊዜ በተለያዩ ብሔረሰብ አባላት ላይ ሲወሰዱ የነበሩትን በኃይል የማፈናቀል እርምጃዎች የተለያዩ ብሔረሰብ አባላት አጥብቀው ሲኮንኑ መደመጣቸው ወደአንድነት የሚያመጣና የሚያበረታታ እንቅስቃሴ ነው። በቋንቋ በብሔር ወዘተ... ልዩነት ላይ ተመሥርተው የሚደረጉ ግጭቶችን ለማጥፋት በተለያዩ የብሔረሰብ አባላት መካከል አንድነት እንዲፈጠር ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት መደረግ ይኖርበታል። ከዚህ ጋር ተያይዞም በሥልጣን ላይ ያለውን የወያኔ ቡድን ከትግራይ ብሔረሰብ አባላት ጋር ደብልቆ የመመልከቱና በዚያ ላይ ተመሥርቶ ጥላቻ የማስፋፋቱ እንቅስቃሴ መወገድ እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህ ጠባብ ቡድን በትግራይም ጭምር ሕዝባዊ መሠረት የሌለው፣ የትግራይም ሕዝብ እንደሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ጠባብ ቡድን የሚረገጥና የሚጨቆን መሆኑን ተገንዝቦ ከትግራይ ሕዝብ ጋር የትግል አንድነት መመስረት ወሳኝ መሆንኑ ማመን ይገባል።

ልዩነታችን ጌጣችን ነው፤ ኢትዮጵያዊነትም የጋራ ቅርሳችን ነው። ይህ የጋራ ታሪካዊ ቅርስ እንደ አትክልት በየጊዜው ውሃ ካልጠጣ ካልተኮተኮተ ይጠወልጋል፤ ይደርቃል፤ ይሞታል። የጋራ ቤታችን ጌጣችንና ቅርሳችን የሆነውን አንድነታችንን ኮትኩተን ካላለመለምን በጋራ የመኖር፤ በሰላም የመኖር በጋራ የመበልጸግ በጋራ የማደግ ተስፋችን ይሟጠጣል። ስለሆነም የጋራ ቤታችንን በጋራ ጥረታችን እንጠብቀው!!

በእኩልነት ላይ በተመሠረተ አንድነታችን የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ይከበራል!!

እናቸንፋለን !!